የሰ/መ/ቁ. 69428

የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ ነገረ ፈጅ አቶ ነጌሣ አሊ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1- መሐመድ አባ አሊ
2- ዘሀራ አባኑር } አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ አመልካች እንዲከፍል የሰጡትን ውሣኔ ህጋዊነት አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ አመልካች ለሞራል ካሣ በድምሩ ከአንድ ሺህ ብር በላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪዎች ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

እኛም ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ አመልካች የተጠሪዎች ልጅ በመሞቱ ምክንያት እንዲከፍል የተወሰነበትን የካሣ ገንዘብ በተመለከተ ለሰበር ችሎት ጭብጥ ሆኖ ያልቀረበ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ የፀናና ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡

የሞራል ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የሚከፈለው የካሣ መጠን በማናቸውም ሁኔታ ከብር አንድ ሺህ ብር /ብር 1000/ መብለጥ የሌለበት መሆኑን "የጉዳት ካሣውም በማናቸውም ምክንያት ከብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ የበለጠ ሊሆን አይችልም" በማለት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2116 ንዑስ አንቀፅ 3 ይደነግጋል፡፡ ይህም በአደጋው ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ብዙ ቢሆንም ለእነርሱ የሚከፈለው የሞራል ካሣ ተደምሮ ከብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ ሊበልጥ የማይገባው መሆኑን ያሣያል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ልጃቸው በአደጋው በመሞቱ ምክንያት ለደረሰባቸው የሞራል ጉዳት ለእያንዳንዳቸው ብር 1000/ አንድ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 2000 /ሁለት ሺህ ብር/ አመልካች የሞራል ካሣ እንዲከፍል

የሰጠው ውሣኔ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2116 ንዑስ አንቀፅ 3 አስገዳጅ ድንጋጌን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ብር 52,200 /ሃምሣ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ብር/ ካሣ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ በድምሩ ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ ብቻ የሞራል ካሣ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ